# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 324 ሐምሌ 18 2006


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የወያኔ የአፈናና የመጨቆኛ መዋቅሮች የህወሓት አባላት በሆኑ የትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት የሚዘወሩ መሆኑ እውነት ነው። ይህ ማለት ግን ህወሓት የትግራይ ሕዝብ ወኪል ወይም ጠበቃ ነው ማለት አይደለም። ትግላችን ከወያኔ ፋሽስታዊ አገዛዝ ጋር መሆኑ እና የትግራይ ሕዝብ የዚህ ትግል አጋር፣ የውጤቱም ተጠቃሚ መሆኑ ማስረገጥ ተገቢ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ሰሜን ሸዋ መርሃቤቴ ዉስጥ የወያኔ ሚሊ ያና ህዝብ አሁንም እንደተፋጠጠ ነዉ

በሰሜን ሸዋ ዞን የመርሃቤቴ ወረዳ ህዝብ ከፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ሚሊሻዎች ጋር ከባድ ግጭት ውስጥ መግባቱን ተከትሎ እስካሁን ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ የወረዳው ነዋሪዎች በአገዛዙ ቅጥረኛ ሚሊሻዎች በጥይት ተደብድበው ሲገደሉ በአገዛዙ በኩል 11 ቅጥረኛ ሚሊሻዎች መገደላቸውን የውስጥ ምንጫችን አመልክቷል። ለግጭቱ መንስኤ እንደሆነ የተነገረው ለመርሃቤቴ አካባቢ መብራት አገልግሎት ይሆን ዘንድ የተላከ ትራንስፎርመር ባልታወቀ ምክንያት በጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት ትዕዛዝ ትራንስፎርመሩን ወደሌላ አካባቢ ሊወስዱት ሲሞክሩ የወረዳው ህዝብ በጋራ ንቅናቄ ፈጥሮ በመውጣት ትራንስፎርመሩን አላስነካም በማለቱ እንደሆነ ታውቋል። ይሁን እንጅ አንዳንድ ነዋሪዎች ለዘጋቢያችን የሰጡት መረጃ እንደሚያመለክተው የወረዳ ህዝብ ላለፉት በርካታ አመታት በከፍተኛ የነፃነት፤ ፍትህና መልካም አስተዳደር እጦት እየተሰቃየ እንደሚገኝና በወረዳው የአገዛዙ ቅጥረኛ ሚሊሻዎችም ያለምንም ከልካይ ንፁሃን ዜጎችን እየገደሉ እንደሚሰውሩ ለማወቅ ተችሏል። አሁን ላይ የተከሰተው ችግር የታፈነው የወረዳው ህዝብ ቁጣ ገንፍሎ እንዲወጣ እንዳስቻለው በስፋት ተነግሯል። በፋሽስቱ ወያኔ እየተገደልን፤ እየተጨቆንን መኖር ይብቃን በማለት ወረዳውን እየሸሹ የተለያዩ የጦር ሃይሎችን ለመቀላቀል የሚሸፍቱ ዜጎች ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣቱን ከዘጋቢያችን መረጃ ለማወቅ ተችሏል። በግጭቱ የቆሰሉ በርካታ ዜጎችም ወደ ሆስፒታል ሲጋዙ መመልከታቸውን የአይን እማኞች አመልክተዋል። ውጥረቱ አሁንም ድረስ እንደቀጠለ ሲሆን ፋሽስቱ ወያኔ ተጨማሪ የጦር ሃይል ወደ አካባቢው ማንቀሳቀሱም ታውቋል። ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ የሟቾቹ ቁጥር እንደሚጨምርም ተመልክቷል።

## የወያኔ ዘረኞች አኬልዳማ ሁለትን ለመስራት ተዋንያንን ማሰልጠን መጀራቸዉ ተሰማ

የወያኔው ጉጅሌ አገዛዝ የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ስም ለማጉደፍ የተለመደውን የኢቲቪ ሀረካት ወይም አኬልዳማ ለመስራት የተለያዩ ግለሰቦችን በማባበል እና በማሰልጠን ላይ መሆኑ ከአዲስአበባ የደረሰን መረጃ አመለከተ።

በህውአት የደህንነት ሰራተኞች ስልጠና የሚሰጣቸው ግለሰቦች በኤርትራ ከሱ ጋር አብረው እንደነበሩና በአቶ አንዳርጋቸው ስብእና ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ እንዲያካሂዱ የተነገራቸው ሲሆን እነኚሁ ግለሰቦች ከሌሎች የኢቲቪ ሰራተኞችና ግለሰቦች ጋር እንዳይገናኙ መደረጉ ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔው አገዛዝ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አፍኖ እያሰቃየ ያለበትን ቦታ በከፍተኛ ሚስጥር መያዙና ከሚመለከታቸው የጉጅሌው ዘረኞች ውጭ ለሌሎቹ ያገዛዙ ባለስልጣን ተብዬዎች እንኳን የተሰወረ መሆኑ የደረሰን መረጃ ጨምሮ ገልጿል።

የፋሺስቱ ወያኔ አገዛዝ ወደ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍሎች ከፍተኛ የሆነ የጦር መሳርያና የሰራዊት ሃይል በማጓጓዝ ላይ መሆኑ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መረጃ አመለከተ። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ በልዩ ደህንነት ስራዎች የሚያሰለጥናቸዉ የፖሊስ ሃላፊዎች አሰልጣኞቻቸዉን ግራ የሚያጋባ ጥያቄ ጠየቁ

ዘረኛዉ የወያኔ ዘገዛዝ ከቀን ወደ ቀን እያደገ የመጣዉን ህዝባዊ አለመረጋጋት ለመቆጣጠር በሚየስችለዉ መልኩ በተለያየ ቦታ የሚያሰልጥናቸዉ የፖሊስ አባለት ከዚህ በፊት ወያኔ ተጠይቆ የማያዉቀዉን ጥያቄ መጠየቅ መጀመራቸዉን ከአዲስ አበባ የሚደርሱን መረጃዎቹ ያሳያሉ። በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ስር በየደረጃው የሚገኙ የፖሊስ ሃላፊዎች ካለፈው አንድ ወር ጀምሮ በሰንዳፋ እና በኮልፌ ፖሊስ ማሰልጠኛዎች ከደህንነት ጋር በተያያዘ ስልጠና እየተሰጣቸው ሲሆን፣ ስልጣ ቹ የሚያነሱዋቸውን ጥያቄዎችን አሰልጣኞች መመለስ አለመቻላቸውን በስልጠናው ላይ የሚሳተፉ ፖሊሶች ለዘግጅት ክፍላችን በላኩት መልዕክት ገልጸዋል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔ አገዛዝ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አስመለክቶ የሰጠው መልስ የእንግሊዝ የፓርላማ አባላትን አስገረመ

በቅርቡ የእንግሊዝ መንግስት አቶ አንዳርጋቸዉን ያሉበት ቦታ ድረስ ሄዶ ማየት እንዲችል ለወያኔ አገዛዝ ያቀረበዉን ጥያቄ አስመልክቶ ከወያኔ ባለስልጣኖች ያገኘዉ መልስ ብዙዎችን እያነገረ መሆንን ከየስፍራዉ የሚደርሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ። የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይና የጋራ ብልጽግና መስሪያ ቤት ዋና ጸሃፊ የሆኑት ማርክ ሲሞንድ የግንቦት7 ዋና ጸሃፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ከእንግሊዝ መንግስት የኮንሱላር ምክር የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች የሚጠይቅ ደብዳቤ ለንደን ለሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ ከሰሞኑ ለጻፉት ደብዳቤ ባገኙት ምላሽ በከፍተኛ ደረጃ መገረማቸዉንና አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌን ጨምሮ ብዙ ኢትዮጵያዉያን ሸብረተኞች ተብለዉ መኮነናቸዉ ጥያቄ እንደጫረባቸዉ ተናግረዋል። በተለይ ለንደን የሚገኘው የወያኔ ኢምባሲ በሰጠው መልስ፣አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በኢትዮጵያ ፓርላማ አሸባሪ የተባለ ድርጅት መሪ መሆናቸውን ገልጾ፣ ለዚህም እንደመረጃ አድርጎ ግንቦት7 በቅርቡ ያወጣውን መግለጫ በእንግሊዝኛ ተርጉሞ አያይዞ አቅርቧል። ይህንን የተተረጎመ መግለጫ ያነበቡ የእንግሊዝ ከፍተኛ ባለስልጣኖችና የፓርላማ አባላት ወያኔ ሽብርተኛ እያለ ፍርድ ቤት ወስዶ ዕድሜ ልክ የሚፈርድባቸዉ ዜጎች ህጋዊና ሠላማዊ ዜጎች መሆናቸዉን በሚገባ መረዳት ችለናል ብለዋል። በተለያ እንድ ባልደረባችን በቅርብ ያናገራቸዉ የእንግሊዝ ፓርላማ አባል ኢትዮጵያ ሽብርተኛ እያለች ዜጎችን የምታስረዉ በእንደዚህ አይነት ምክንያቶች ከሆነ ዝንግሊዝ ከዚህ አገዛዝ ጋር ያላትን ግኑኝነት መፈተሽ አለባት ብለዋል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የጎንደር ህዝብ ኃ/ማሪያም ደሳለኝን በጥያቄ አፋጠጠ፤ የአስተዳደር በደል አንደሚደርሰበትም ተናገረ

በዚህ አመት የጎንደር ዩኒቨርስቲ የምረቃ ስነስርአት ላይ ለመገኘት ወደ ስፍራዉ አቅንቶ የነበረዉ የወያኔዉ ተላላኪ ጠ/ሚኒስቴር ኀ/ይለማርያም ደሳለኝ እግረምነገዱን ከከተማውና ከአካባቢው ህዝብ ተወካዮች ጋር ባደረገዉ ዉይይት ከህዘብ የቀረቡለትን ያልተጠበቁ ጥያቄዎች መመለስ አቅቶት ግራ እንደተጋባ ዉይይቱን በስፍራዉ ሆነዉ የተከታተሉት ዉስጥ አዋቂ ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። በዚህ ህዝቡ በድፍረት ያሉበትን የመልካም አስተዳደርና ልማት ችግሮች ዘርዝሮ ባቀረበበት ዉይይት ላይ ጠ/ሚኒስቴር ተብዬዉ እንድም ጥያቄ አግባብ ባለዉ መልኩ ሳይመልስ ወደመጣበት መመለሱን ምንጮቻችን አክልዉ ገልጸዋል። አንድ አስተያየት ሰጪ፣ "ከጎንደር አየር ማረፊያ እስከ አዘዞ ያለው መንገድ እናንተ ትማጣላችሁ ተብሎ በአፈር ተደለደለ እንጅ መኪና አያሳልፍም ነበር" ብለዋል። "ውሃንም በተመለከተ አላህ አልፎ አልፎ ዝናብ እያዘነበልን ነው እንጅ አንገረብን የመሰለ ውሃ እያለ በውሃ ጥም እናልቅ ነበር፣ ግማሹን ማህጸነ ሰፊ ግማሹን ማህጸነ ጠባብ እያደረጉት ነው " በማለት አስተያየት ሰጪው አክለዋል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ሰራዊት ወደ ሰሜን እያጓጓዘ መሆኑ ተሰማ

አገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገሮች በህዝብ ተግልና በራሱ ዉስጥ በተፈጠረዉ ቀዉስ ክፉኛ የተደናገጠዉ የወያኔ አገዛዝ እጅግ በጣም ብዙ ወራዊትና መሳሪያ ወደ ሰሜናዊዉ የአገራችን አካባቢዎች በመላክ ላይ መሆኑን ከሰሜን ሸዋ፤ ጎንደር፤ ጎጃም፤ ወሎና አስብ የሚደርሱን መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይ በቅርቡ የወያኔ ከፍተኛ የደህንነት አባላት በጠ/ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ያደረጉትን ስብሰባ ተከትሎ፣ ወያኔ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የሰራዊቱንና ከባድ መሳሪያዎችን በምሽት ወደ ሽሬ፣ ተከዜ፣ ወልቃይት፣ መተማ፣ አርማጭሆ በመሳሰሉት የሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል እያጓጓዘ ነው። ሁሉንም ነገር በመሳሪያ ደፍጥጦ ማጥፋት የሚችል የሚመስለዉ ወያኔ ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ መታፈን ጋር በተያያዘ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተቀሰቀሰዉን ህዝባዊ ቁጣና በየቦታዉ የተነሳበትን ተቃዉሞ ለማጥፋት በሚል ሰራዊቱንና ደህንነቱን የቦታዉ በእያሰማራ ነው።

ከሰሜን አካባቢዎች የመጡ የደህንነት አባላት፣ ግንቦት7 ከኤርትራ መንግስት ጋር በመተባበር ለአርሶ አደሩ የጦር መሳሪያ በማደል እስከ መሃል አገር ሊገባ ይችላል የሚል አስተያየት መስጠታቸውን ተከትሎ፣ ግንባሩ በድንበር አካባቢዎች ላሰማራቸው የድርጅቱ አባላት ባለሀብቶች ዘመናዊ ስልኮችን በማደል የስለላ ስራ እንዲሰሩ እንዳሰማራቸው ታውቋል። ከተለያዩ የሰራዊቱ ክፍሎች የሚከዱ ወታደሮች ቁጥር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እየጨመረ በመጣበት በዚህ ወቅት፣ ኢህአዴግ የሚጠፉ ወታደሮችን ለመተካት በሚል ያወጣው የቅጥር ማስታወቂያ የተፈለገውን ያክል የሰው ሃይል አላስገኘለትም። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ለብሔራዊ አንድነትና ነፃነት - ህወሓትን ከትግራይ ሕዝብ መነጠል!!!

በአለፉት ጥቂት ሣምንታት በወያኔ የተፈፀሙ የእብደት ተግባራትን ስናጤን ከፊት ለፊት ኢትዮጵያችንን እየጠበቀ ያለው መንታ መንገድ አመላካች ነው። ይህ ከፊት ለፊት የሚጠብቀን መንታ መንገድ አንዱ ወደ ብሔራዊ አንድነት፣ ነፃነትና ብልጽግና ሌላው ወደ እርስ በርስ ትርምስና ውድቀት የሚያመሩ ናቸው። የአንድነት፣ የነፃነትና የብልጽግና መንገድ ለመያዝ መስመራችንን ማስተካከል ያለብን ከአሁኑ ነው።

ለመሆኑ ከላይ ያልነውን ለማለት ያስቻሉን በአለፉት ጥቂት ሣምንታት በወያኔ የተፈፀሙት ተግባራት ምንድናቸው?

**አንደኛ፤** ወያኔ፣ ዓለም ዓቀፍ ህግንና ሥርዓትን በጣሰ መንገድ ከየመን ባለሥልጣናት ጋር በማበር የንቅናቄዓችንን ዋና ፀሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ማፈኑ በአለፉት ጥቂት ሣምንታት ውስጥ ውስጥ የተደረገ አብይ ክስተት ነው። ይህ የወያኔ የውንብድና ተግባር ኢትዮጵያዊያንን በእጅጉ አስቆጥቷል። ወያኔ፣ ለሀገር ነፃነትና ለእኩልነት የሚታገልን አንድ ታላቅ ሰውን ማፈንኑና ከእይታ ከልሎ እያሰቃየው መሆኑ በሕዝቡ ውስጥ ያለው ቁጣ ወደ መገንፈል አስጠግቶታል። አቶ አንዳርጋቸው በጠላት እጅ ከወደቀም በኋላ ኢትዮጵያዊያንን አሰባሳቢ ኃይል ሆኗል።

**ሁለተኛ፤** ሰላምተኞቹን ብሎገሮችንና ጋዜጠኞችን በሽብርተኝነት በመክሰስ በቋፍ ላይ የነበረውን የወጣቶች ትዕግሥት እንዲሚጠጥ አድርጓል። ስለኢንተርኔት አጠቃቀምና ጥንቃቄ ሥልጠና መውሰድ በክስ ቻርጁ ውስጥ መካከቱ ሥርዓቱ ከእውቀት ጋር የተጣላ መሆኑ በግልጽ አሳይቷል። ከዚህም በተጨማሪ በህጋዊ ፓርቲዎች ውስጥ በንቃት የሚሳተፉ ወጣት መሪዎችን መርጦ በማሠርና በሽብርተኝነት በመወንጀል የወያኔ የአፈና መዋቅር ወጣቱ ላይ ማነጣጠሩ ግልጽ ሆኗል።

**ሦስተኛ፤** እጅግ ሰላማዊና ጨዋነት በተሞላበት መንገድ አቤቱታቸውን በማቅረብ ላይ የነበሩትን ሙስሊም ወገኖቻችንን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በመደብደብ እና በጅምላ በማሠር በወያኔ መድብለ ቃላት ውስጥ "ሰላማዊ ትግል" የሚባል ነገር አለመኖሩ፤ ተቃውሞ ሁሉ "ሽብር" እንደሚባልና በሽብርተኝነት እንደሚያስከስስ በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጧል። ይህም የሥርዓቱ አውሬዓዊ ባህሪ መገለጫ ሆኗል።

**አራተኛ፤** አፈናውና እስሩ ወደ ትግራይም በመዛመቱ ወያኔ የቆመበት ምድር እየራደ መሆኑ አመላካች ሆኗል። ትግራይ ውስጥ የነበረው አፈና ድብቅ የነበረ ከመሆኑም በላይ ከወያኔ የውስጥ ሽኩቻ ጋር ሲያያዝ ቆይቷል። አሁን ግን ሁኔታዎች እየተቀየሩ ነው። አገራዊ ርዕይ ያነገቡ፤ ወያኔን በጽናት ለመታገል የቆረጡ የትግራይ ወጣቶች ወደፊት እየመጡ ነው። እነዚህ ወጣቶች የተጫነባቸውን ድርብርብ ጫና በመበጣጠስ ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ወገናቸው ጎን መቆማቸውን በተግባር እያረጋገጡ፤ ለዚህም መስዋዕትነት እየከፈሉ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩት አራት ጉዳዮች በጋራ ሲታዩ የተበታተነ የሚመስለው እና በተለያዩ ስልቶች የሚደረገው ትግል የሚሰባሰብበትና የሚቀናጅበት ወቅት ላይ መደረሱ አመላካቾች ናቸው። ዛሬ የምንገኘው የተለያዩ የትግል ስልቶች እንዲናበቡና እንዲደጋገፉ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ የሆነበት ወቅት ላይ ነው።

በተለይም ወያኔ፣ መሸሸጊያ ምሽጉ አድርጎ በሚቆጥረው ትግራይ ውስጥ እየዳበሩ የመጡት የአመጽም አመጽ-የለሽ ትግሎችም አስተዋጽኦ ከፍተኛነት ሌላው ኢትዮጵያዊ እንዲረዳ ማድረግ ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው። የወያኔ የአፈናና የመጨቆኛ መዋቅሮች የህወሓት አባላት በሆኑ የትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት የሚዘወሩ መሆኑ እውነት ነው። ይህ ማለት ግን ህወሓት የትግራይ ሕዝብ ወኪል ወይም ጠበቃ ነው ማለት አይደለም። ትግላችን ከወያኔ ፋሽስታዊ አገዛዝ ጋር መሆኑ እና የትግራይ ሕዝብ የዚህ ትግል አጋር፣ የውጤቱም ተጠቃሚ መሆኑ ማስረገጥ ተገቢ ነው።

ከፊት ለፊታችን ካሉት መንታ መንገዶች መካከል የአንድነትን፣ የነፃነትና የብልጽግናን መንገድ ለመምረጥ የትግራይ ሕዝብ በስፋት ትግሉን እንዲቀላቀል ማድረግ ተገቢ ነው። ትግራይ የህወሓት የግል ጓዳ መሆኗ የማብቂያ ጊዜ ማፋጠን ይቻላል። በዲሞክራሲያዊ ትግል ውስጥ ያሉ ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ የጋራ ግንዛቤ ከያዙ ወያኔን ማንሳፈፍ የሚቻልበት እድል በስፋት ተከፍቷል።

ስለሆነም፣ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዘረኛውና ፋሽስታዊው ህወሓትን ከትግራይ ሕዝብ መነጠል አንዱ የትግላችን ስትራቴጂ ሊሆን ይገባል ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የወያኔ ዘረኞች አኬልዳማ ሁለትን ለመስራት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የፋሺስቱ ጉጅሌ አገዛዝ የግንቦት 7 ንቅናቄ የሰሜኑን አካባቢ ህዝብ አደራጅቶ ጥቃት ሊያደርስብኝ ይችላል የሚል ስጋት ያደረበት በመሆኑ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊትና ከባድ የጦር መሳሪያዎችን ወደ ሽሬ ተከዜ ወልቃይት መተማ እና አርማጭሆ አካባቢ በማጓጓዝ ስራ ላይ ተጠምዶ መሰንበቱ ታውቋል:: የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ በፋሺስቱ ዘረኛ ቡድን መታፈን በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ እና ቁጭት መፍጠሩ በተለያዩ፣ ማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎችና የዜና አውታሮች መገለጹን ተከትሎ የወያኔው ጉጅሌ አገዛዝ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መውደቁና የህውአት የደህንነት አባላትም ጥቃት ሊሰነዘርባቸው ይችላሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ቦታዎችን በከፍተኛ ወታደራዊ ሃይል ማስጠበቅና በህብረተሰቡ ውስጥ የተለመደውን ሽብር በመፍጠር ህዘቡን ለማስፈራራት የተለያዩ፣ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻዎችን ለማካሄድ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ከውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ያገኘነው መረጃ አመልክቷል:: ይህ በንዲህ እንዳለ በፋሺስቱ አገዛዝ የጦር መሪዎች በስልጣን መባለግና ንቅዘት እንዲሁም ዘረኝነት እና አድልዎ ከፍተኛ ቅሬታ ያደረበት የሰራዊት ክፍል የመዋጋት ፍላጎቱ የላሸቀና በአለቆቹም ላይ እምነት ማጣቱ በሰፊው እየተነገረ ሲሆን ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ወታደሮች እና ባለሌላ ማእረግተኞች አገዛዙን በመክዳት ወደ ተቃዋሚ ሃይሎችና ወዳልታወቀ ስፍራ በመሄድ ላይ መሆናቸው ተዘግቧል::

## የጎንደር ህዝብ ኃ/ማሪያም ደሳለኝን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አንድ ከበየዳ ወረዳ የመጡ ሰው ደግሞ ወረዳው መብራት እንዳልገባለት ፣ በየአመቱ በርካታ የመንግስት ሰራተኞች እየፈለሱ መሆኑን በያዝነው አመት ብቻ 141 መምህራን ከወረዳው መፍለሱን ተናግረዋል። ወጣቶች መሬት በማጣታቸው ማህበራዊ ችግሮች እየተፈጠሩ መሆኑን ግልጸዋል።

በጎንደር ከፍተኛ የመንገድ ችግር እንዳለ የገለጹት አንዲት ተናጋሪ፣ በከተማው ስላለው ውሃ ሲናገሩ ደግሞ "ምግብ በልተን ውሃ መጠጣት የማችልበት ደረጃ ደርሰናል" ብለዋል። "ጎንደር ተረስታለች" ያሉት ተናጋሪዋ በከተማዋ የመልካም አስተዳደር ችግር አለ ሲሉ አክለዋል። አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ የመስራት ፍላጎት ቢኖርም አቅም አለመኖሩን፣ አቅምም ቢኖር የአመለካከትና የአፈጻጸም ችግር መኖሩን ተናግረዋል። በሌላ ዜና ደግሞ በሞያሌ ከተማ ውሃ ከጠፋ 1 ወር መሙላቱን የአካባቢው ነዋሪዎች ለኢሳት ገልጸዋል። በደብረማርቆስ ከተማ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የስኳር እጥረት ማጋጠሙን ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

## ወያኔ በልዩ ደህንነት ስራዎች የሚያሰለጥናቸዉ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ፖሊሶቹ "መንግስት በተለይ ከሙስሊም ሃይማኖት ተከታዮች የሚነሳውን ዲሞክራሲያዊየሆነጥያቄለምንአይመልስም?ለምን በፖሊስ ተቋም ላይ የስራ ጫና እንዲበዛ ይደረጋል? ህዝቡ በፖሊስ ላይ ያለውጥላቻ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፣ እኛ ህብረተሰቡን በተገቢው መንገድ ማገልገል እንፈልጋለንና አስተዳዳራዊ ሁኔታዎች ይለወጡ" የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል። አሰልጣኞቹ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ከአቅማቸው በላይ መሆኑንና የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣኖች የሚመልሱዋቸው እንደሆነ እየገለጹ ነው። በሚሰጠው መልስ ደስተኛ ያልሆኑት ፖሊሶች፣ ትክክለኛውን መልስ የሚሰጠው አካል ይመጣል ብለው ቢጠባበቁም እስካሁን ድረስ አርኪ መልስ የሚሰጥ ባለስልጣን አላገኙም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከፌደራል ጉዳዮችና ኢህአዴግ ጽ/ቤት በተላለፈ ትዕዛዝ መሰረት በአዲስ አበባ በሁሉም ክ/ከተማዎችና በ116 ወረዳዎች የሚኖሩሙ ስሊም ኢትዮጵያውያንን ለማደን እንቅስቃሴ እንዲጀመር ትእዛዝ መሰጠቱ ታውቋል ትእዛዙ የተሰጠው ለሁሉም ከፌደራል እስከ ወረዳ ድረስ ለሚሰሩ የኢህአዴግ አባላት ሲሆን የጽ/ቤት ሃላፊዎች በየጽ/ቤታቸው የሚገኙ አባላትን በመጥራት ስለወጣው ትእዛዝ ገልጸውላቸዋል። የቀበሌ መታወቂያ የሌለው ሙስሊም ታፍሶ እንዲታሰርና ወደመጣበት አካባቢ እንዲሸኝ ይደረጋል። ይህንን ልዩ ተልዕኮ የሚመሩት በየክ/ከተማውና በየወረዳው የሚሰሩ በጥቅም የተሳሰሩ ሙስሊሞች ናቸው ሲሉ ምንጮች አክለዋል። ባለፉት 3 ቀናት የተለያዩ የደህንነት አባላት በሚያውቋቸው ሙስሊሞች ዘንድ በመደወል ለማስፈራራት መሞከራቸውን የኢሳት ምንጮች ገልጸዋል።

ባለፈው አርብ ኢህአዴግ የጸጥታ ሃይሎች በረመዳን ጾም ላይ በሚገኙት ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ላይ የወሰዱት እርምጃ ጥቁር ሽብር ተብሎ መሰየሙ ይታወቃል። ኢህአዴግ የጸጥታ ሃይሎች በቀሰቀሱትግጭት በርካታ ሙስሊሞች ተደብድበው ሆስፒታል የገቡ ሲሆን፣ በብዙ መቶወች የሚቆጠሩት ደግሞ ታስረው ከፍተኛ የሆነ ስቃይ ከደረሰባቸው በሁዋላ ብዙዎቹ ተለቀዋል። በተለይ በሴቶች ላይ የተወሰደው እርምጃ አስከፊ እንደነበር የሚወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ።

## ለማነዉ የምትዋጋዉ? ማንንስ ነዉ የምትዋጋዉ?

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ እሱን ከመሰለ ህዝብን ከማይወክል ከሃዲ የየመን አገዛዝ ጋር በመመሳጠር የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ጸሐፊ የሆኑትን አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌን በቁጥጥሩ ስር ማድረጉ የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት ሃምሳ አመታት ባልታየ መልኩ ከዳር ዳር ተነሳስቶ "እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ" እያለ ህዝባዊ ትግሉን እንዲቀላቀል አድርጎታል። ባለፈዉ የአንድ ወር ግዜ ዉስጥ ከተላላኪዉ ጠ/ሚኒስቴር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ እስከተባባሪዉ ጠ/ሚኒስቴር ዴቪድ ካምሪን፤ ከለንደኑ ዘጋርዲያን እስከ ዋሺንግተን ዲሲዉ ዋሺንግተን ፖስት ድረስ አንዳርጋቸዉ ጽጌ የአለም ጋዜጦችና መንግስታት የመነጋገሪያ አርዕስት ሆኖ ሰንብቷል። እርግጠኞች ነን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላትም የዚህን ጀግናና የአገር አለኝታ የሆነ ሰዉ በዘረኞች እጅ መዉደቅ የሰሙና የተነጋገሩበት ይመስለናል። ለመሆኑ ወያኔዎች በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር የአገርና የህዝብ ገንዘብ ለወንጀላቸዉ ተባባሪ ለሆነ አገር ከፍለዉ አንዳርጋቸዉ ጽጌን የያዘዉ ለምንድነዉ? መልሱ ቀላል ነዉ። አንዳርጋቸዉ ጽጌ የወያኔን ዘረኝነት፤ መብት ረገጣና የጅምላ ግዲያ የሚቃወም ብቻ ሳይሆን እነዚህን አስከፊ ገጽታዎችና እነሱን ይዟቸዉ የመጣዉን የወያኔን ስርዐት ከምድረ ኢትዮጵያ ጠራርጎ ለማጥፋት ተግባራዊ እንቅስቃሴ የጀመረ ጀግና ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ነዉ። አንዳርጋቸዉ ጽጌ በአገር መከላከያ ሠራዊት ዉስጥ ወያኔ የዘረጋዉ የዘረኝነት መረብ ለአገራችን አንድነት አደጋ መሆኑንና በተለይም በመከላከያ ሠራዊት ዉስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑ የበላይ መኮንኖች የሚታዘዙና በቁራኛ የሚጠበቁ መሆናቸዉን አጥብቆ የሚቃወም አርቆ አሳቢ ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ነዉ። ጠቅለል ባለ መልኩ ወያኔዎች አንዳርጋቸዉን ያሰሩት በአንዳርጋቸዉ መወገድ እነሱ የመከላከያ ሠራዊቱን በዘርና በቋንቋ ከፋፍለዉ ኣትዮጵያን እንዳሰኛቸዉ የሚዘርፉና ዳር ድንበሯንም ባሰኛቸዉ ግዜ ሁሉ ለጨረታ ማቅረብ የሚችሉ መስሏቸዉ ነዉ።

ወያኔ አገር ዉስጥና በአለም ዙሪያ ኢትዮጵያዉያን በሚኖሩባቸዉ ቦታዎች ሁሉ ያሰማራቸዉ ካድሬዎች ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት የወያኔን የበላይነት፤ አይደፈርነትና ኃይለኝነት ሲሰብኩ ከርመዋል። ለመሆኑ ወያኔ እዉነትም እንደሚነገርለት ኃይለኛ ነዉ? ሀይለኛ ከሆነስ ከዬት ነዉ የወያኔ ኃይል የሚመነጨዉ? የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት በሙሉ በያላችሁበት ደግማችሁ ደጋግማችሁ ይህንን ጥያቄ እራሳችሁን ልትጠይቁና መልሱንም እራሳችሁ ልትመልሱ ይገባል። እንደፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በ2011 ዓም የግብጽ ህዝብ እርግጫና እስር በቃ ብሎ ጣሂሪር አደባባይ ሲወጣ ሆስኒ ሙባረክ እንደለመደዉ የጸጥታ ኃይሎቹን ልኮ ሠላማዊ ሠልፈኞችን ለመግደል ሞክሮ ነበር።ሆኖም ሂዱና ግደሉ የሚለዉን አምባገነናዊ ትዕዛዝ አልቀበልም እኔ የቆምኩት ለአምባገነኖች ሳይሆን ለግብጽ ህዝብ ነዉ ብሎ ሙባረክን ፍጻሜና የግብጽን ትንሳኤ ያፋጠነዉ የግብጽ መከላከያ ሠራዊት ነበር። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የአገርና የህዝብ አለኝታነቱን ከግብጽ መከለያከያ ሠራዊት ይማራል የሚል እምነት የለንም፤ ሆኖም ዛሬ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሚመራዉና የግዳጅ ትዕዛዝ የሚሰጠዉ በኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ነዉና የሆስኒ ሙባረክን የግደሉልኝ ትዕዛዝ አልቀበልም ያለዉን የግብጽን መከላከያ ሠራዊት የቅርብ ግዜ ልምድ ቀና ብሎ መመልከቱ ጠቃሚ ይመስለናል።

ተከታታይ ትዉልድ ባደረገዉ ተጋድሎ ከ3ሺ አመታት በላይ ዳር ድንበሯ ተከብሮ የኖረችዉ እናት አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ የምትገኝበትን ሁኔታ ከመከላከያ ሠራዊታችን በላይ የሚያዉቅ ኢትዮጵያዊ ተቋም ያለ አይመስለንም። ይህንን አደገኛ ሁኔታ ለመቀየርና ኢትዮጵያን የእኩሎች አገር በማድረጉ ዘመቻም ከዚሁ መከላከያ ሠራዊታችን ዉጭ ዉሳኙን ሚና መጫወት የሚችል ተቋም የለም። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የአገሩን ዳር ድንበር ሊቆርሱ የመጡ ወራሪዎችን አይቀጡ ቅጣት መቅጣት ነዉ የሚያዉቅበት እንጂ የአገሩን ዳር ድንበር ቆርሰዉ ለባዕዳን የሚሰጡ ወንበዴዎች መጠቀሚያ መሳሪያ አይሆንም፤ ሆኖም አያዉቅም። የ1996ቱ አብዮት እንደሚያስታዉሰንም የፊዉዳሉን ስርዐት በቃህ ብሎ የመጨረሻዉን በትር ያሳረፈበት በወቅቱ የነበረዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ነበር። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት "የአገር መከላከያ ሠራዊት" ተብሎ የሚጠራዉ በዚህ አገራዊ ተቋም ዉስጥ በመደራጀቱ ብቻ አየደለም። ይህ ሠራዊት ኢትዮጵያዊ እናት፤ አባት፤ወንድም፤ እህት፤ አያት ፤ አጎትና አክስት አለዉ። መሳሪያ አንግቦ በየዱሩና በየሸለቆዉ ደሙን የሚያፈስሰዉም ለእነዚሁ ቤተሰቦቹ፤ ዘመዶቹና ወዳጆቹ ሲል ነዉ እንጂ በዘር ከፋፍሎ ለሚገዛዉና ወንድሞቹንና እህቶቹን ለሚገድል ዘረኛ ስርዐት ዕድሜ መራዘም አይደለም። በተለይ ዛሬ በከፍተኛ ደረጃ የተማሩና አገራችንን ወደፊት ማራመድ የሚችሉ ዜጎች መኖሪያ ማዕከላዊ፤ ቃሊቲ፤ ሸዋ ሮቢትና ቂሊንጦ እስር ቤቶች ዉስጥ በሆነበትና ኢትዮጵያዊነትን የሚሰብኩ ሰዎች በወያኔ ካድሬዎች እንደ አዉሬ ታድነዉ በሚገደሉበት ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አይደለም የበዳዮችና የዘረኞች መሳሪያ መሆን ይህ በደል በወንድሞቹና በእህቶቹ ላይ ሲደርስ በፍጹም ዝም ብሎ መመለከት ለበትም። መከላከያ ሠራዊታችን ዛሬ አገራችን ከምትገኝበት የታሪክ ምዕራፍ አኳያ እኔ ከዚህም ከዚያም አይደለሁም የሚል ተቋም አይደለም። የህዝብ ልጅና የአገር ጠባቂ ነዉና ምንግዜም ቢሆን ሽንጡን ገትሮ መቆም ያለበት ከህዝብ ጎን ብቻ ነዉ። ለህገ መንግስት መገዛትና የበላይ አለቆቹን ትዕዛዝ ማክበር የማንም መከላከያ ሠራዊት ተቀዳሚ ሀላፊነት እንደሆነ እንረዳለን፤ ሆኖም ትዕዛዝ ሰጪዎቹ ፀረ ህዝቦች ሲሆኑና እነሱ እራሳቸዉ ለህገመንግስቱ የማይገዙ ሲሆኑ የመከላከያ ሠራዊት የእንደዚህ አይነቶቹን ጋጠወጦች ትዕዛዝ በፍጹም መስማት የለበትም፤ የሱ ቃልኪዳን ለአገሩና ለህግ መንግስቱ ነዉ እንጂ እሱን እራሱን በዘር ከፋፍለዉ ለሚረግጡት የወያኔ ዘረኞች አይደለም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት የወያኔን ስርዐት በተለያየ መልኩ ታግሏል፤ ዛሬም እየታገለ ነዉ። ሆኖም ወያኔንና ወያኔ የፈጠረዉን ዘረኛ ስርዐት አስወግዶ በምትኩ ህዝባዊ ስርዐት መፍጠር አልቻለም። ለዚህ ህዝባዊ ጥረት አለመሳካት ብዙ ምክንያቶችን መደርደር ይቻላል- ዋናዉ ምክንያት ግን ወያኔ የአገር መከላከያ ተቋምን የሱን ዘረኛ ስርዐት ብቻ በሚያገለግልበት መልኩ መቅርጽ በመቻሉና በሲቪል ቢሮክራሲ ዉስጥም ለሆዳቸዉ ብቻ ያደሩ ምስለኔዎችን ከጎኑ ማሰለፍ በመቻሉ ነዉ። ይህ ሃያ ሁለት አመት ሙሉ አጃችንን አጣጥፈን የተመለከትነዉ ሐቅ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን ሌላ ሐቅ አለ፤ እሱም በወያኔ የምንረገጠዉ እኛ ወያኔ እኛን ረግጦ እንዲገዛ ኃይል የሆንነዉም እኛዉ እራሳችን መሆናችንን ነዉ። ከዚህ አንደ ሀሞት ከሚመር ሐቅ አስተዋዩና የአገር መከታ የሆነዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ብዙ የሚማራቸዉ ቁም ነገሮች አሉ ብለን እናምናለን። ለምሳሌ በአንድ በኩል እሱ እራሱ በየቀኑ በወያኔ ዘረኞች የሚረገጠዉ ኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ወያኔን እየከዳ ወይም የወያኔን ስርዐት ከዉስጥ እያፈረሰ ለህዝብ መብትና ነጻነት መከበር የቆሙ ኃይሎችን ቢቀላቀልና ባዕዴን፤ ኦህዴድና ደህዴግ ዉስጥ የሚገኙ ዛሬም ልባቸዉ ከኢትዮጵያ ህዝብ ልብ ያልተለየ ወገኖች ኢህአዴግ የሚባለዉን በቅርጽም በይዘትም ባዶ የሆነ የጠላት መሳሪያ የሆነ ድርጅት እየለቀቁ ቢወጡ ወያኔ የሚተማመንበት አግአዚ ጦር ይህንን ዘረኛ ስርዐት ለአንድ ቀንም መሸከም አይችልም። ስለዚህ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ከዛሬ ጀምሮ ለእናት አገሩ ዳር ድንበር መከበር፤ ለወገኖቹ መብት መከበርና ለራሱ ታሪክና ክብር ሲል የወያኔን ስርዐት ቢቻል ዉስጥ ሆኖ ማፍረስ አለበት፤ አለዚያም ይህንን የወያኔን በዘር የተደራጀ መከላከያ ተቋም እየለቀቀ ለአገር ፤ ለወገን መብትና ለእኩልነት የቆሙ ኃይሎችን ያሉበት ቦታ ድረስ እየሄደ መቀላቀል አለበት። እነዚህ ነገሮች የማድረግ ችሎታ የሌለዉ የሠራዊቱ አካል ወይ ሠራዊቱን ከድቶ መዉጣት አለዚያም ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትን ነጻነት መከበር በሚታገሉ ኃይሎች ላይ እርምጃ እንዲወስድ የሚሰጠዉን ወያኔያዊ ትዕዛዝ በፍጹም መቀበል የለበትም።

ከኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የወጣኼዉ ዉድ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ሆይ ወደድክም ጠላህ ዛሬ ወያኔ አባቶችህን በመጦሪያቸዉ እያሰረ የሚያዋርዳቸዉ፤ ወንድሞችህን ብልታቸዉ ላይ ጠርሙስ እያንጠለጠለ የሚያሰቃያቸዉና እህቶችህን ጡታቸዉን በጉንጥ እየቆነጠጠ ደም እምባ የሚያስነባቸዉ ባንተ ትከሻ ላይ ተፈናጥጦ ነዉ። አንተ ወግድ ብለህ ብትከዳዉ ወያኔ በራሱ ይህ ነዉ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል ኃይል የሌለዉ ባዶ ድርጅት ነዉ። ወያኔ ህዝብ ወድዶና ፈልጎ የመረጠዉ አካል ስላልሆነም ከህዝብ የመነጨ ኃይል የለዉም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ህገመንግስቱን እንዳሰኘዉ የሚደፈጥጥ ጀብደኛ ድርጅት ነዉና ህግ የሚገዛዉ ኃይልም የለዉም። ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎ እየረገጠ፤ እያሰረና እየገደለ የሚገዛዉ የኢትዮጵያን መከላከያና ፖሊስ ሠራዊት ተቋሞች ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር ስላደረገ ብቻ ነዉ። ወያኔ እነዚህ ህዝብን ለማሸበር የሚጠቀምባቸዉን አገራዊ ተቋሞች የሚያስተዳድራቸዉ በህጋዊ መንገድ ሳይሆን ያዉ አንደለመደዉ እነሱንም በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎ ወርቃማዉ ዘር እያለ የሚጠራዉን እየሾመና እየሸለመ ብዙኋኑን መለዮ ለባሽ ደግሞ እንደ ተራ የቤት ዉስጥ አገልጋይ እየረገጠ ነዉ።

ታድያ አገሩንና ወገኑን ከጠላት ለመታደግ ቃልኪዳን የገባዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ለምንድነዉ በአንድ በኩል እሱ እራሱ እንደ መሬት እየተረገጠ በሌላ በኩል ደግሞ ወገኖቹን እያሰረና እየገደለ ለሚገዛ ዘረኛ ስርዐት መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለዉ? እስከመቼ ነዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እነ ወይንሸት ሞላ፤ ርኢዮት አለሙ፤ ኤዶም ካሳዬና ማህሌት ፋንታሁን 'ወንድም ጋሻ" ድረስልን ብለዉ ሲጣሩት እሱ የወያኔ ጋሻ ሆኖ የእህቶቹን ጩኸት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የሚመለከተዉ? አረ እስከመቼ ነዉ እነ አቤል ዋበላ፤ ናትናኤል ፈለቀ፤ ዘላለም ክብረትና ተስፋ አለም ወልደየስ ማዐከላዊ እስር ቤት ዉስጥ በወያኔ አዉሬዎች ቆዳቸዉ ሲፋቅና ጥፍራቸዉ ሲነቀል አገሩንና ወገኑን ለመጠበቅ ቃል ኪዳን የገባዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዝም ብሎ የሚመለከተዉ? እርግጠኞች ነን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ አለዉ፤ እንዲህ ብለን በድፍረት የምንናገረዉ ደግሞ ለይስሙላ ሳይሆን ሰራዊቱ ከኛዉ አብራክ ዉስጥ ተከፍሎ የወጣ የሰራ አካላችን ነዉና ለአፍታም የማንጠራጠረዉ እዉነት ስለሆነ ነዉ።

ዛሬ ያለንበትን ግዜና ወያኔ በወገንና በአገር ላይ የሚያደርሰዉን በደልና ግፍ ስንመለከት ቁም ነገሩ መልስ መኖሩና አለመኖሩ ላይ አይደለም። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የወገኖቹን የድረሱልኝ ጥሪ ሰምቶ በወያኔ ላይ አስፈላጊዉን እርምጃ መዉሰድ ያለበት ነገ ሳይሆን ዛሬ በኋላ ሳይሆን አሁን ነዉ።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የታዋቂው ፖለቲከኛና ጸሃፊ አብርሃ ደስታ እህት ከስራ ታገደች

ባለፉዉ ሳምንት የአቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌን እህት በሀያ አራት ሰዐት ግዜ ዉስጥ ከአገር ያባረረዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በዚህ ሳምንት ደግሞ የታዋቂዉን ታጋይና የዓረና ፓርቲ አባል የአቶ አብርሃ ደስታን እህት ከስራ ማባረሩ ተገለጸ። ከአረና የወጣው መረጃ እንደሚያሳየው ወይዘሪት ተክለ ደስታ የኣብራሃ ደስታ እህት በመሆንዋ ብቻ ከስራዋ ታግዳለች። ወይዘሪት ተክለ ደስታ የጤና ባለሙያ ስትሆን የህወሓት ኣባልና የራያ ዓዘቦ ወረዳ የጤና ፅህፈት ቤት ምክትል ሃላፊ ሆና ታገለግል ነበር።

የወረዳው ባለስልጣናት "አንቺ እንደ ወንድምሽ ዓረናነሽ፣ ላንቺ የሚሆን የህወሓት ሃላፊነትም ይሁን የሞያ ስራ የለንም፣ ላንቺ እንኳን ስራ፣ መሬቱም እሳት ሆኖ ያቃጥልሻል " በማለት ከስራዋም ከህወሃት አባልነትም እንዳባረሩዋት ድርጅቱ አስታውቋል። የህወሓት ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ኣባይ ወልዱ ታላቅ ወንድም የሆነው ኣቶ ኣውዓሎም ወልዱ የዓረና መስራችና ኣመራር ኣባልነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ወይዘሮ ኣልጋነሽ ገብሩ በህወሓት መንግስት "ኣሸባሪ" ተብላ ከተከሰሰች ጀምሮ 3ቱ ህፃናት ልጆቿ የጎዳና ሂወት መምራት መጀመራቸውን ከድርጅቱ የተገኘው መረጃ አመልክቷል። ህፃናቱ ኣባታቸውን ከ9 ዓመትበፊትበሞትያጡሲሆኑ፣ ጠላ እየጠመቀች ታስተዳድራቸው የነበረችው እናታቸውን በእስር ምክንያት ካጡ ብኋላ ትምህርታቸው ኣቋርጠው፣ የጎዳና ሂወት መግፋት ጀምረዋል። እናታቸውበ"ኣሸባሪነት" ተፈርጃ በእስር ያጡህፃናትን ለመንከባከብ በህብረት ባንክ መቐለ ቅርንጫፍ በ202 041 606 379 3018 የሚልየአካውንት ቁጥርተከፍቷል። የሂሳብ ደፍተሩ የተከፍተው በወይ ዘሮ ኣልጋነሽ ታናሽ እህት ወይዘሮ ፅጌ ገብሩ ነው።

## የአለም ባንክ ጥናቶች ኢትዮጵያ የኤክስፖርት ዘርፍ እጅግ በጣም ደካማ መሆኑን አመለከተ

የአለም ባንክ በአጭር ግዜ ዉስጥ ለሦስተኛ ግዜ ባካሄደዉ ጥናት በወያኔ ቁጥጥር ስር የምትገኘዉ ኢትዮጵያ ባለፉት አስር አመታት ዉስጥ በዬትኛዉም መለኪያ እጅግ በጣም ዝቅተኛ የወጪ ንግድ አፈጻጸም ማስመዝገቧን አመለከተ። በባንኩ ዋና ኢኮኖሚስትና የፕሮግራም መሪ የሆኑት ዶ/ር ላርስ ክርስቲያን ሞለር፣ «ባለፉት 18 ወራት በተለይ አገሪቱ እያሽቆለቆለ የመጣ የወጪ ንግድ ውጤት አስመዝግባለች፤» ብለዋል። ቀድሞውንም ለውድድር ተጋላጭ በሆኑ የግብርና ውጤቶች ላይ የተመሠረተው የአገሪቱ ኤክስፖርት ዘርፍ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም ላይ በታየው የሸቀጦች ዋጋ መቀነስ የተነሳ፣ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባቱ ነው አስከፊ የተባለውን አፈጻጸም ያስመዘገበው። ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ያሳየው ለውጥ ከሁለት እስከ ሦስት ከመቶ ዝቅ ያለ መሆኑን፣ ዓምና ጭራሽ ከዜሮ በታች አሽቆልቁሎ እንደነበርም ባንኩ አስታውሷል።

87 በመቶ የሚደርሱት ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ከአነስተኛ ገንዘብ አቅራቢዎች የብድር አቅርቦት እንደሚያገኙ፣ ከ94 በመቶ በላይ የሚሆኑት ትልልቅ ድርጅቶች ደግሞ ባንኮች ፋይናንስ እንደሚያደርጓቸው የባንኩ ጥናት ያመለክታል። በሁለቱ መካከል የሚገኙት አነስተኛና መካከለኛ ድርጅርቶች ግን ብድር እያገኙ እንዳልሆነ ተጠቁሟል። መሀል ላይ የተረሱ ወይም «ዘ ሚሲንግ ሚድል» በሚል በባንኩ የተገለጹት ድርጅቶች ከባንክ የሚያገኙት ፋይናንስ ስድስት በመቶ ብቻ መሆኑን፣ ከአነስተኛ የገንዘብ ድርጅቶች ብድር የሚያገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ደግሞ 11 ከመቶ ናቸው። ይህ በመሆኑም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ወደላይ እንዳያድጉና ኤክስፖርት ዘርፍ ላይ እንዳይሳተፉ ችግር ሆኖባቸዋል ተብሏል። «ተወዳዳሪነትን በማሻሻል የኤክስፖርት አፈጻጸምን ማጠናከር» የሚል ርዕስ የተሰጠው የባንኩ ጥናት ይፋ የተደረገው ሐምሌ 15 ቀን 2006 ዓ.ም. በሸራተን አዲስ ነበር። ላለፉት ዘጠኝ ወራት ሲጠናቀር የቆየው የባንኩ ኢኮኖሚክ ሪፖርት፣ አገሪቱ ያላት የኤክስፖርት ዘርፍ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ለመዋቅራዊ ለውጥ አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳልቻለና በአንፃሩ በምሥራቅ እስያ ላሉት አገሮች የአምራች ኢንዱስትሪው የኤክስፖርት ዕድገት መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት መቻሉን ያስገነዝባል።

«የአገሪቱ የሸቀጥ ምርቶች በፋብሪካ ሳይቀነባበሩ ለውጭ ገበያ ይቀርባሉ፤» ያለው ባንኩ፣ በዚህ የተነሳም ከጥራትና ከምርት ውስብስብነት ይልቅ ዘርፉ በዋጋ ላይ ጥገኛ እንዲሆን እንዳስገደደውም ገልጿል። «ለአብነት ለውጭ የምታቀርበው ቡና በፀሐይ ከሚደርቅ ይልቅ በውኃ ታጥቦ የሚደርቅ በመሆኑ በዓለም ገበያ ታገኝ የነበረውን ጥቅም እያሳጣት ይገኛል» ያሉት ዶ/ር ሞለር፣ የተቆላ ቡና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ቢቻል ደግሞ 200 ፐርሰንት የዋጋ ጭማሪ ሊገኝ ይችል እንደነበርም ይፋ አድርገዋል። የአበባ ዘርፍ ከፍተኛ ጥራት ባላቸው ማሽኒያዎች ቢጠቀም ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ማግኘት የሚችልበት ዕድል እንዳለው ሲገለጽ፣ ቆዳ በእጅ ከሚለፋ ይልቅ በማሽን እንዲለፋ ቢደረግ ከ20 እስከ 30 በመቶ የዋጋ ጭማሪ ያስገኝ ነበር ተብሏል።

በባንኩ ጥናት መሠረት በኢትዮጵያ ኤክስፖርት የሚያደርጉ ድርጅቶች ብዛት 1,825 ነው። ከዚህ ባሻገር ወደ ኤክስፖርት ዘርፉ የሚገቡ ድርጅቶች ጋሬጣ የሚበዛባቸው በመሆኑ፣ ዘርፉ በፍጥነት እንዳይለወጥ ምክንያት መሆኑን ባንኩ በጥናቱ አስታውቋል። «አነስተኛ ድርጅቶች በቂ የፋይናንስ አቅርቦት ሊያገኙ አለመቻላቸው አንዱ ጋሬጣ ነው፤» ያሉት ዶ/ር ሞለር፣ ከነባር ድርጅቶች ይልቅ ከታች በፍጥነት እያደጉ የሚመጡ ድርጅቶች ዕድሉን ቢያገኙ፣ አዳዲስ የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ የተሻሉ ይሆኑ እንደነበርም አስታውቀዋል። ባንኩ የንግድ ሎጂስቲክስ ትልቁ ችግር ሆኖ መቀጠሉን ሲያትት፣ በአሁኑ ጊዜ ከጂቡቲ ወደብ ወደ መሀል አገር ዕቃዎችን ለማጓጓዝ ከ40 ቀናት በላይ እየወሰደ እንደሚገኝና የንግድ ተወዳዳሪነትም በዚህ ችግር ምክንያት አረንቋ ውስጥ መግባቱን አስፍሯል። ባንኩ ከለያቸው ችግሮች ውስጥ የፋይናንስ አቅርቦት፣ መሬት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የንግድ ቁጥጥርና ታክስ ዋና ዋና የሚባሉት መሆናቸውን አመልክቷል።

የኤክስፖርት ዘርፉን ለማሻሻል መንግሥት ከትክክለኛው ዋጋው በላይ የሆነውን የምንዛሪ ተመን እንዲያስተካክል ባንኩ ጥሪ አቅርቧል። መንግሥት ለዚህ ጥሪ ምላሹ አጭር ነበር። የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ዴኤታው አቶ አህመድ ሺዴ እንደተናገሩት፣ መንግሥት የዋጋ ግሽበትና የአገሪቱ ዕዳን ስለሚያባብስበት የገንዘብ ምንዛሪ ተመንን ለገበያ ክፍት እንደማያደርግ አስታውቀዋል። ባንኩ በሚያቀርበው መከራከሪያ መሠረት ኢትዮጵያ ያለባትን የውጭ ምንዛሪ ችግር ለመፍታትና በኤክስፖርት ገበያው ተወዳዳሪ ለመሆን፣ ምርቶቿን በርካሽ ለመሸጥ የብርን የመግዛት አቅም ከሌሎች መገበያያ ገንዘቦች አኳያ ዝቅ እንዲል ማድረግ ይጠበቅባታል።

ይህም ማለት አንድ ዶላር ለማግኘት አሁን ከሚከፈለው ሃያ ብር ይልቅ ይበልጥ እንዲሆን ማድረግ ማለት ነው። ለአብነት አንድ ዶላር ለማግኘት የሚወጣውን ሃያ ብር ወደ 30 ብር ከፍ እንዲል በማድረግ የኤክስፖርት ሸቀጦችን በርካሽ ዋጋ አብዝቶ ለመሸጥ ያስችላል። በሌላ በኩል እንዲህ ያለው የምንዛሪ ለውጥ የገቢ ንግድን ውድ ከማድረጉም በላይ በዋጋ ግሽበት ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ቀላል ባለመሆኑ፣ መንግሥት ይህንን በመፍራት ከኤክስፖርት ይልቅ በማክሮ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች ላይ ማተኮርን እንደመረጠ ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀዋል። ሪፖርቱ ይፋ ሲደረግ የተገኙ የመንግሥት አካላት፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ተሳታፊዎች ባንኩን የሚሞግቱ ጥያቄዎችን አቅርበዋል።

የኤክስፖርት ዘርፍ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት አኳያ የሚያደርገው አስተዋጽኦ 14 በመቶ ሲሆን፣ ይጠበቅ የነበረው ግን 24 በመቶ ነበር። ምንም እንኳ ባንኩ የኤክስፖርት ዘርፉ ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አኳያ ያለውን አፈጻጸም የመዳሰስ ዳራ ባይኖረውም፣ አገሪቱ ባለፉት ሦስት ዓመታት ያሳየችው ዝቅተኛ አፈጻጸም፣ በአሥር ዓመት ውስጥ ከታየው ይልቅ ዝቅተኛው ነው ተብሏል። መንግሥት በዚህ ዓመት ከአምስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ከወጪ ንግድ ይጠብቅ የነበረ ቢሆንም፣ በአሥር ወራት ውስጥ የተገኘው ግን ከ2.6 ቢሊዮን ዶላር አልዘለለም። ይህም ቢሆን ግን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአገሪቱ የኤክስፖርት መጠን ውስጥ አንድ ሦስተኛውን አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ የዓለም ባንክ አስታውቋል። በዚህ መደሰታቸውን የገለጹት የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተወልደ ገብረ ማርያም፣ የአየር መንገዱ አስተዋጽኦ በአግባቡ ሲታይ እንዳልቆየና ምሥጋና እንደማይቸረው ተናግረዋል። የዓለም ባንክ ይፋ ያደረገውን ጥናት ተከትሎ በርካታ ጥያቄዎችና ክርክሮች ተደምጠዋል።

## ዳንሻና ጸገዴ ዉስጥ የብአዴንና የህወሃት ታጣቂዎች ተፋጥጠዋል

የትግራይ ክልል ባለስልጣናት በጸገዴ ወረዳ አካባቢ የሚገኙ በአማራው ክልል ስር ተካለው የሚገኙ በርካታ ቀበሌዎችን መውሰዳቸውንተከትሎ ፣ የአማራ ክልል ታጣቂዎች ድርጊቱን በመቃወም ከትግራይ ክልል ታጣቂዎች ጋር ተፋጠው እንደሚገኙና በማንኛውም ሰአት ግጭት ይፈጠራል ተብሎ እንደሚፈራ የአካባቢው ነዋሪዎች ለኢሳት ገልጸዋል። ወደ 400 የሚጠጉ የአማራ ክልል ታጣቂዎች ወደ ድንበሩ የተጠጉ ሲሆን፣ በትግራይ ክልል በኩል ምን ያክል ታጣቂዎች እንደተሰለፉ ለማወቅ አልተቻለም። የመከላከያ ሰራዊት ሆነ የፌደራል ፖሊስ አባላት በአካባቢው አይታዩም። አልፎ አልፎ የተኩስ ድምጽ እየተሰማ መሆኑንም ነዋሪዎች አክለው ገልጸዋል። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች በብአዴንና በህወሃት ታጣቂዎች መካከል የተጀመረው ግጭት እየሰፋ ሂዶ ኢህአዴግን ሊበትነው ይችላል በማለት እየተናገሩ ነው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ወያኔ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ሰራዊት

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

የኢህአዴግ ሰራዊት በከፍተኛ የሞራል ውድቀት ላይ መሆኑን የሚናገሩት ከሰራዊቱ የሚከዱ ወታደሮች፣ በዘር ላይ የተመሰረተው አደረጃጃት፣ የምግብ አቅርቦት መበላሸት እና የሰራዊቱ የኑሮ ሁኔታ ማሽቆልቆል ለሰራዊቱ ሞራል መውደቅ ዋና ምክንያቶች ሆነው ይጠቀሳሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢህአዴግ የመከፋፈል አደጋ እንዳንዣበበት ምንጮች ገልጸዋል የገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር በተለይ ከአቶ መለስ ሞት በኃላ አገሪትዋን መምራት ካለመቻሉ ጋር ተያይዞ በዜጎች ላይ የሚወስደው የጅምላ እስርና የማሳደድ ዘመቻ በራሱ አባላት ጭምር ጥያቄ እያስነሳ መሆኑ ተሰምቷል። ፓርቲዎች በሽብርተኛነት ሰም ፖለቲከኞችንና ጋዜጠኞች ላይ ያነጣጠረ የእስር እርምጃ አጠናክሮ መቀጠሉ በተለይ መካከለኛና ዝቅተኛ አመራሩ አካባቢ ተቃውሞና ጉምጉምታ እየተሰማ ነው። ምንጮች እንደገለጹት በኢህአዴግ በኩል የሚወሰደው ኢ-ዴሞክራሲያዊ እርምጃ የህዝብ አመኔታ በማሳጣት የግንባሩን ሕልውና ችግር ላይ ይጥላል የሚሉእና እየተወሰደ ያለውን ጉልበት የታከለበት እርምጃ በሚደግፉ አባላትና ከፍተኛ ካድሬዎች መካከል መቃቃር እየተፈጠረ መሆኑ ታውቋል። ግንባሩ በተፈጥሮው ከግምገማ በዘለለ የውስ ጥቅራኔን የሚፈታበት መንገድ የሌለው መሆኑና ልዩነቶች ከባድ ዋጋ የሚያስከፍ ሉበመሆናቸው ምክንያት ቅሬታዎቹ ታምቀው እስካሁን መቆየታቸውን የገለጹት ምንጮቻችን በተለይ በሠላማዊ መንገድ ቅሬታውን ከሁለት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ እየገለጸ ያለውን ሰፊ የሙስሊም ማህበረሰብ የተቃውሞ ድምጽ ለማፈን ኃይል የታከለበት ተደጋጋሚ እርምጃ በረመዳን የጾም ወር መወሰዱ ሙስሊም የግንባሩን አባላት ጨምሮ በበርካታ አባላት ዘንድ ተቃውሞ እንዲቀጣጠል ምክንያት መሆኑ ታውቋል። ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት ከተቃዋ ሚፓርቲዎች፣ ከጋዜጠኞች፣ከሲቪል ማህበረሰብ አባላት፣ ከሙስሊሙ ህብረተሰብ፣ በብዛት ወጣቶችን ካቀፈው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ማህበረ ቅዱሳን እንዲሁም በኑሮ ውድነት ከሚሰቃየው ሰፊ ህብረተሰብ እና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመላተሙ በመጪው ምርጫ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሊመረጥ እንደማይችል መገንዘቡን ያስታወሱት ምንጮቹ በዚህ የተነሳ የትኛውንም ዓይነትተ ቃውሞ በኃይል ለመደፍጠጥ ወስኖ ተግባራዊ በማድረግ ላይ መሆኑን አስታውሰዋል። ይህ የግንባሩ እርምጃ ትክክል አይደለም የሚሉ አባላት ብቅ ብቅ ማለታቸው ግንባሩ በቀጣይ ከባድ የመሰነጣጠቅ አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል የመጀመሪያው ምልክት መሆኑንምንጮቹ ጠቁመዋል።

## የወያኔ አገዛዝ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አስመለከቶ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ግንቦት 7 አቶ አንዳርጋቸውን ለማስፈታት በኢትዮጵያ፣ በየመን እና በእንግሊዝ መንግስታት ላይ ኢትዮጵያውያን መውሰድ ስላለባቸው  እርምጃዎች የሚዘረዝር መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል። በመላው አለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በእንግሊዝ ኢምባሲ ፊት ለፊት በመሄድ ተቃውሞ እንዲያሰሙ፣ ተከታታይ ደብዳቤዎችን እንዲጽፉ የሚጠይቀውን መግለጫ፣ ግንቦት7 አሸባሪ ድርጅት ለመሆኑ ማሳያ ነው በማለት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የጻፈው ደብዳቤ የፓርላማ አባላቱንና የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሰራተኞችን እንዳስገረማቸው ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ የአቶ አንዳርጋቸው ቤተሰቦች ገልጸዋል። የአቶ አንዳርጋቸውን ጉዳይ በቅርብ የሚከታተሉት ሁለቱ የፓርላማ አባላት ጀርሚ ኮርቢን እና ኤምሊ ቶርንቤሪ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በሰጠው መልስ ከተገረሙት መካከል ሲሆን፣ ባለስልጣኖቹ የእንግሊዝ መንግስት በሂደት ስለሚወስደው እርምጃ እንዲብራራላቸው ደብዳቤ ጽፈዋል። የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ዋና ጸሃፊ፣ አገራቸው በተከታታይ ስለምትወስደው እርምጃ ዝርዝር መርሃ ግብር እያዘጋጁ መሆኑን ለፓርላማ አባላቱ ገልጿል። ኢሳት ባለስልጣኖቹ የተጻጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ቅጅ የደረሰው ሲሆን፣ ከደብዳቤዎች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ መንግስት በአቶ አንዳርጋቸው ላይ የሚያቀርበው የሽብርተኝነት ክስ  ግንቦት 7 መንግስትን በሃይል አወርዳለሁ ብሎ ማወጁ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአቶ አንዳርጋቸው ጉዳይ አሁንም የመነጋጋሪያ አጀንዳ እንደሆነ ቀጥሎአል። በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖሩ ዜጎች ስልኮችን ለኢሳት በመደወል ለአቶ አንዳርጋቸው ያላቸውን አክብሮትና መካሄድ ስላለበት ትግል አስተያየቶችን ይሰጣሉ።

## ለማነዉ የምትዋጋዉ? ማንንስ ነዉ የምትዋጋዉ?

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በመካከሉ እንደ እንክርዳድ  ሆን ተብሎ ተዘርቶ የበቀለ አግአዚ የሚባል ከመግደል ዉጭ ሌላ ምንም የማያዉቅ የአረመኔዎች ክምችት እንዳለ እናዉቃለን። ሆኖም ዛሬ ግዜዉና አጋጣሚዉ የአግዘዚ ሳይሆን የእኛ ነዉ። የትግራይ ህዝብን ጨምሮ መላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በጀግንነት የቆመዉ ከአግአዚ ጋር ሳይሆን ለመብቱና ለነጻነቱ ከሚታገሉ ወገኖች ጎን ነዉ። ስለዚህ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ታሪክ፤ እዉነት፤ንጹህ ህዝባዊ አላማና የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎኑ ናቸዉና ወያኔን ከድቶ የነጻነት ኃይሎችን መቀላቀል ምንም የሚያስፈራዉ ነገር የለም።

ከዛሬ በኋላ የመከላከያ ሠራዊታችን ተቀዳሚ ተግባር በአንድ አላማ ስር ተሰልፎና እንደ አንድ  ሰዉ በህብረት ቆሞ የወገኖቹን መብትና እኩልነት ማስከበር፤የአገሩን ዳር ድንበር መጠበቅ፤ በተለይም ለእናት አገሩ ዳር ድንበር መከበር የተዋደቁ አባቶቹና አያቶቹ አጽም ያረፈበትን ቦታ ምን ግዜም ቢሆን የኢትዮጵያ መሬት አካል መሆኑን ማረጋገጥ ነዉ።